# “የፌደራል ስርአት ጉዳይ ለድርድር አይቀርብም”-ኦዴፓ ከአስመሳይ ተራማጅነት ወደ ፍጹም አምባገነንነት!

(እያሱ ወልደ-ነጎድጓድ)

የኢትዮጵያ ህገ-መንግስትና የፌደራል ስርዓት የኢትዮጵያ ህዝብ የመከረበትና ይጠቅመኛል ብሎ ያጸደቀው አይደለም። ህወሓት ሀገሪቱን በወረሃ ግንቦት1983ዓ.ም እንደተቆጣጠረ ቀደም ሲል ደረግ ከሻቢያና ከወያኔ ጋር ሲዋጋ ዳናው ተሰምቶ የማይታወቀው ኦነግ ከኤርትራ ተስፈንጥሮ አዲስ አበባ ገባ። በዚህም ኢትተጵያም በሶስት ክፉ ጠላቶች ስር ወደቀች፡- ህወሓት፣ ሻእቢያና ኦነግ። በዚህ ወቅት ኢትየጵያን ወደ ሞት ከሚወስዷት አውሬዎች የሚከላከል ሌላ ሃይል አልነበራትም። አፍቃሪ ኢትዮጵያውያንም እንደተለመደው አዲስ ኃይል ሲመጣ መጨብጨቡን ቀጠሉበት።

ሦስቱ አውሬዎች ኢትዮጰያን ለማጥፋት የነደፉት የጥፋት ስልት በዘር ላይ የተመሠረት የፌደራል ሥርዓት መመሠረትና ለዚህም ግብዓት የሚሆን ጸረ-ኢትዮጵያ የሆነ ህገ-መንግስት መቅረጽ ነበር። የጸረ-ኢትዮጵያው ህገ መንግስት ዋና ግቡ ለኢትዮጵያ ህልውና መሠረት የሆኑ ነገሮችን በሙሉ መደምሰስ ነበር/ነውም። በዚህም መሠረት ኢትዮጵያን ከስር መሠረቷ ለማናጋት ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች ተቀመጡ። ብሄረን ከብሄር በቋሚነት የሚያጋጩ የጎጥ አስተዳደር፣ ሁለተኛ ለኢትዮጵያ አንድነት ከፍተኛ አስተዋፆ አለው የሚሉትን ቡድን በሁሉም መስክ ማዳከምና ሰስተኛው ለኢትዮጵያ አንድነት አስተዋጾ የሚያደርጉ እሳቤዎችን/እምነቶችን ማጥፋት ናቸው።

የቋንቋ/ዘር-ፌደራሊዝም፡-ኢትዮጵያውያን እርስ በርሳቸው ብሄር ሳይገድባቸው እጅግ የተደበላለቁ በመሆኑ የዘር-ፌደራሊዝም የሚመጥናቸው አልነበረም። ነገር ግን ኢትዮጵያውያን ተገደው በቋንቋ እንደ ዳቦ ተከፋፈሉ። ጸረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ዋና ግባቸው ኢትዮጵያዊነትንና ለኢትዮጲያ ከፍተኛ አስተዋጾ ያደርጋል የሚሉትን ኃይል መግደል በመሆኑ ቋንቋን እንደመስፈርት እዚህ ላይ አይጠቀሙም፤ የተጠቀሙትና የሚጠቀሙት ኃይል ነው። የወልቃይት፤የራያና የሸዋ አማራን ጉዳይ በምሳሌት መውሰድ ይቻላል።

በዚህ የዘር ፌደራሊዝም መሰረት ከ1984ዓ.ም ከበደኖና አርባ ጉጉ የአማሮች ጭፋጨፋ ጀምሮ እስከ አሁኗ ሰዓት ድርስ ለሩብ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያዊያን እርስ በርስ እየተገዳደሉ ይገኛሉ። ብሄረን መሠረት ያደርገ ከቀየ መፈናቀል፤ መገድል ንብረትና ሀብትን መዘረፍ የኢትዮጵያውያን የሩብ ክብለ ዘመን ቋሚ ክስተት ሆኗል። የቋንቋ ፌደራዝም እስካለ ድርስ ይህ ክፉ ድርጊት ይቀጥላል ምን አልባትም ለኢትዮጵያ ህልውና ማክተም ዋና ምክንያት ሊሆን ይችላል።

ሁለተኛው ኢትዮጵያን የመግደያ ስልት ለኢትዮጵያ ደህንነት አስተዋፆ የሚያደርጉ እሳቤዎችን/እምነቶችን ማደከም ነበር/ነው። በዚህ በኩል ለጸረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ዋና ጠላት ሆና የተገኘችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ኃይማኖት ናት። ለዚህም ነው ህወሓት ኦርቶዶክስን እንደ ኳስ ሲጫወትባት የኖረው። አሁንም እንዚህ ጸረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች የቤተ ክርስቲያን መዋቅሩንና ኃይማቱን ከማናጋት አልፈው ቤተክርስቲያናትን እያቃጠሉ የሚገኙት።

ሦስተኛው ለኢትዮጵያ አንድነት ከፍተኛ አስተዋፆ አለው የሚሉተን ቡድን በጭክነት ማጥቃት ነው። በዚህ በኩል ዋና ኢላማ የሆነው አማራ ነው።ጸረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች አማራን አቅም አልባ/ሽባ ለማድረግ የተጠቀሙበትና የሚጠቀሙባቸው ስልቶች ብዙ ናቸው። የኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዳይሆን የህዝብ ቁጥር መቀነስ፤ ጸረ-አማራ የሆኑ ቡድኖች ክልሉን እንዲመሩ መመደብ፤ በተለያዩ የፈደራል መስሪያቤቶች ተገቢውን ውክልና እንዳያገኝ መከልከልና በዋናት የአማራን ታሪካዊ ረዕስቶች መከፋፈል ናቸው።

በኢትዮጵያ የአማራን ታሪካዊ ርዕስቶች ያልተከፋፈለ ክልል አለ ለማለት አያስደፍርም። በዋናነት ግን የአማራ ዕርስቶች የተከፋፈሉት ህወሃትና ኦነግ ናቸው። ህወሓት ከትግራይ የራቀውን የአማራ ዕርስት ለሌሎች ያከፋፈለበት ትልቁ ምክንያት የአማራን ጠላቶች በማብዛት አማራ በወልቃይትና ራያ ላይ የሚኖረውን ትኩረት ለማሳጣት መሆኑ ግልፅ ነው።

ሥለሆነም የአማራን ታሪካዊ ዕርስቶች ያለ አማራ ውክልና የተከፋፈሉ ኃይሎች (ህወሓትና ኦነግ/ኦዴፓ) የፌደራል ስርዓቱን አንደ አይነ ብሌን እንጠብቀዋለን ቢሉ አይፈረድባቸውም ምክንያቱም ይሕ የዘር ፌደራዝም ለህወሓትና ኦነግ ቀደም ሲል ያልነበራቸውን መሬቶች እንዲዘርፉ እድል የሰጣቸው በመሆኑ።ለዚህም ነው

ኦዴፓ/አነግ በዛሬው እለት (Feb.19/02/2019) "የፌደራሊዝም ስርአት ጉዳይ ለድርድር የሚቀርብ አይደለም" በማለት በትዕቢት መግለጫ ያወጣው።

አስመሳዩና ሸንጋዩ ኦዴፓ ስልጣን በደንብ እስኪቆናጠጥ ድረስ ኢትዮጵያ ሱስ ናት፤ ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞትም ኢትዮጵያ ነን በማለት የዋሕ ኢትዮጵያንን አስጨፈረ፤ ሁሉም የእነረሱን ፎቶ በመኪናውና በቤቱ ለጠፈ። ኦዴፓ/ኦነግ ግን ስልጣን በያዘ ማግስት ወሳኝ የሆኑ የፌደራል ስልጣኖችን ያለምንም ይሉኝታ ለብቻው ተቆጣጠረ፤ አዲስ አበባ የእኛ ናት አለ፤ በአጽሟ የቆመቸው ኢትዮጵያ በኦነግ ስትዘረፍ አይቶ እንዳላየ ዝም አለ፤ በአሸዋ ሜዳ  ዘራፊ ቄሮዎች ህዝብ ሲገድሉ፤ ህፃናትን አስገድደው ሲደፍሩ፤ ንብረት ሲያወድሙ አካባቢው ለጸጥታ ጥበቃ ስለማያመች ነው ብሎ ተሳለቀ። ግፍ የደረሰባቸው ወገኖች ብሶታቸውን ሊያሰሙ ሰልፍ ሲወጡ በግፍ ተገደሉ፤ ወንጀለኛውን ቄሮን ትቶ የአዲስ አበባ ወጣቶችን በጅምላ በማሰር ኦዴፓ የወደፊቱ ከህወሓት የበለጠ ህወሓት እንደሚሆን በተግባር  አሳየ።  ይህ ሁሉ ግፍና አድሎ የሚከናወነው ኦዴፓ ስልጣን ከያዝ በስምንት ወራት ውስጥ ነው። በዚህ ፍጥነትም ይሕ ድርጅት ሱሴናት ያላትን  ኢትዮጵያ ለማፍረስ  ሁለት ዓመት የሚወስድበት አይመስለኝም።

ኦዴፓም ሆነ ህወሓት ያልተገነዘቡት አንድ ትልቅ ነገር ቢኖር በ21ኛ ክፍለ ዘመን የሌላወን ታሪካዊ እርስት በጉልበት ቀምቶ መሄድ የማይቻል መሆኑን ነው። እንገነጠላለን ካሉ መገንጠል የሚችሉት የአማራን ርእስቶች በመነጠቅ ሳይሆን የራሳቸውን ዕርስት በመያዝ ነው። ይህ አካሄድ ግን ለኦዴፓ እጅግ አደገኛ ነው ምክንያቱም የእኔ ነው የሚለው ታሪካዊ እርስት ስሌለለው። ነገ ሌላ ቀን ነውና ዛሬ ኦዴፓና ህወሓት አለን የሚሉት ጉልበት አማራው እንደሚኖረው መጠራጠር አይኖርባቸውም። እነርሱ በጉልበት የአማራን መሬት ሲነጥቁ አማራ ለዕርስቱ መሰዋት የማይክፍልበት ምክንያት አይኖርም።

**በ21ኛው ክፍለ ዘመን ባርነትንና ውርደትን  የሚያስተናግድ  አካል አይኖርም!**